*የፔን ማኖር [Penn Manor] ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፡-*

*አብዛኛዎቻችሁ እንደምታውቁት፣ ዓርብ ዕለት የግራፍቲ ሥዕል በመታጠቢያ ክፍል ውስጥ ተገኝቷል። ምንም እንኳ በተፈጥሮው አስጊ ይዘት ያለው ቢሆንም በፖሊስም ሆነ በትምህርት ቤቱ አስተዳደር በሁለቱም እንደሚታመን ተደርጎ ሊቆጠር አልቻለም። ሌላ የግራፍቲ ሥዕል በሌላ መታጠቢያ ቤት ሰኞ ዕለት ተገኝቷል።*

*ምስጋና ኃላፊነት ለሚሰማቸው ዛሬ ጠዋት ሪፖርት ያደርጉ ሁለት ተማሪዎች ይሁንና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ አስተዳደር እና የሚለርስቪል ቦሮው ፖሊስ መምሪያ [Millersville Borough Police Department] ለሁለቱም መልእክቶች ኃላፊነቱን የሚወስደውን ግለሰብ በፍጥነት ማወቅ የቻሉ ሲሆን ይኸው ተማሪ በቁጥጥር ሥር ውሏል። ብዕር እና ማስታወሻ ደብተር ብቻ ነበሩ ተማሪው ይዞ የተገኘው።*

*ይህ ተማሪ እነዚህን ሽብር ስጋቶች ሲፈጥር በጣም ደካማ ምርጫ ነው ያደረገው። በማናቸውም ጊዜ ምንም እንኳ የሽብር ጥቃቱ ማስፈራሪያ በጣም ቀላል እንኳ ቢሆን ትምህርት ቤቱ እና ፖሊስ ጉዳዩን በከባድ እንደሚመለከቱት እና የእኛ ትምህርት ቤት ደኅንነት አስተማማኝ መሆኑን እስከምናረጋግጥ ድረስ አስፈላጊው ሁሉ ምርመራ እንደሚደረግ እባካችሁ ተረዱልን። ሁሉም ሰው እያንዳንዳችን የምንናገረው ወይም የምንጽፈው ነገር ከባድ ክብደት እንዳለው እና ከባድ ቅጣትና መዘዝ ሊያስከትል እንደሚችል ልንረዳ ይገባል። የእኛ ፖሊሲ ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር መተባበርን እና ሊወሰድ የሚችለውን ከባድ እርምጃ እንዲወሰድ የሚፈቅድ ነው። የላንካስተር ካውንቲ ዲስትሪክት ዓቃቤ ሕግም እንዲህ የመሰሉትን የጥቃት ማስፈራሪያዎች በከባዱ እንደሚመለከታቸው ልትገነዘቡ ይገባል። አሁን ባለው ጊዜ ላይ የአካባቢ ባለሥልጣናት ይህን የተፈጠረውን ሁኔታ ለመቆጣጠር ከባድ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ናቸው።*

*ክቡራት እና ክቡራን፣ ምን ያክሎቻችሁ በዚህ በተፈጠረው ሁኔታ እንደተደናገጣችሁ እና በፍሎሪዳ የተፈጠረውን ነገር ከግምት ውስጥ በማስገባት የእኛን ትምህርት ቤት ውስጥ ኢደጋ ውስጥ እንዲገባ እንደማትፈልጉ እሙን ነው። ኃላፊነት የሚሰማው እና ለደኅንነት አስተማማኝ የሆነ ትምህርት ቤት እንዳለን እርግጠኛ ለመሆን የሚቻለንን ሁሉ ማድረግ አለብን። ችግር በሚፈጠርበት ጊዜም ችግሩን ተቋቁመን መዝለቅ መቻል አለብን። ቀላል ባይሆንም፣ መረበሽ፣ ጭንቀት ወይም ፍራቻ እኛን እንዲቆጣጠሩን መፍቀድ የለብንም።*

*እርስ በርስ መደጋገፋችንን፣ ማናቸውንም የሚያሳስብ ነገር ሪፖርት ማድረጋችንን እና ትምህርት ቤታችንን ደኅንነቱ አስተማማኝ እንደሆነ ማቆየታችንን እባካችሁ እንቀጥል።*

*ዶ/ር ፊል ጌል [Dr. Phil Gale]*

*የፔን ማኖር [Penn Manor] ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር*